


# ከኦገስት1-31/2025 የነበረዉ የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም ከሴፕቴምበር 1-30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር

2025

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ


ባለፈዉ የኦገስት ወር በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡ ፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ 24 ሰዓት ዉስጥ ከ30ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 32.2፣ 39፣ ሀዋሳ 37፣ አርባምንጭ 40.3፣ ባህር ዳር 42.3፣ 38.1፣ 44.3፣ 68.4፣ 36.8፣ ኮምቦልቻ 66፣ 69.9፣ ቢሾፍቱ 38፣ 31፣ ደብረ ማርቆስ 39.7፣ ድሬዳዋ 40.4፣ 32.8፣ 46.5፣ 45.1፣ ጎንደር 30.3፣ ጎሬ 39.7፣ ጅማ 55.2፣ 32.8፣ መቀሌ 50.4፣ 51፣ መተሃራ 32.9፣ 46፣ 46.3፣ ነቀምት 167.6፣52.8፣ 33.4፣47.7፣ 30.7፣ 47፣ 39.3፣ 37፣ አቦቦ 57.6፣ 34.2፣ አቦምሳ 46፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 46.5፣ 35.3፣ አዴት 41.5፣ 30፣ አደዋ 46.2፣ አዲግራት 40.5፣ 60፣ አይደር 38.3፣ 33፣ አይራ 37.6፣ 31.2፣ 30.2፣ 46.8፣ 32.4፣ ሃሮማያ 40.4፣ 42.2፣ አልጌ 30፣ 50፣ 30 አማን 31.2፣ 65.8፣ 47.6፣ 41.8፣ አምቦ 35.9፣ አምደወርቅ 37.8፣ 39፣ 38.9፣ 32.5፣ 36.8፣ 39.3፣ 37፣ 48.2፣ 37.5፣ አንግር ጉትን 32፣ 34.6፣ አርሲ ሮቤ 39.6፣ አርጆ 32.4፣ 34.2፣ 36.8፣ አሶሳ 38፣ 39.8፣ አጽቢ 33.6፣ 47.5፣ 48፣ አሶሳ አዋሽ አርባ 30፣ አየሁ 36፣ አክሱም 30፣ አይከል 36.1፣ ባቲ 30፣ 59.5፣ ቡሂ 38.2፣ 30.5፣ ቡለን 30፣ 40.2፣ 30.4፣ 40.4፣ 40፣ ቡሬጂ 31፣ ቻግኒ 33.2፣ 50፣ 42.6፣ 37.4፣ ጭፍራ 46.4፣ 70፣ ጭራ 36.2፣ 45፣ ጨፋ 37.4፣ ጨዋቃ 30፣ 45.2፣ 35፣ ዳንግላ 50.5፣ 36፣ 30.6፣ ደባርቅ 51.5፣ 80.6፣ ደብረ ብርሃን 32.7፣ 37.5፣ 32.8፣ 32.2፣ 38.8፣ ደብረ ታቦር 37.9፣ 31.7፣ 33.6፣ 38.2፣ ደብረ ወርቅ 30.7፣ 48.4፣ ዲላ 67.5፣ ኢጃጂ 85.7፣ 77.5፣ እነዋሪ 59.2፣ 37፣ ፍቼ 44.9፣ 34.4፣ 32.2፣ ፉኝዶ 37፣ 56.6፣ ጋምቤላ 40.3፣ 44.7፣ 39፣ 34.8፣ 57.5፣ ጋቲራ 34.5፣ 31.2፣ ገልምሶ 34.5፣ 43.4፣ 48.5፣ ገዋኔ 32.4፣ ወሊሶ 44.6፣ 34፣ ጊዳ አያና 40.9፣ 32፣ ጊምቢ 43.5፣ 38.1፣ 49.5፣ 52.3፣ ጉንዶ መስቀል 32.7፣ 45፣ 30.2፣ 36.6፣ 48.6፣ 32.2፣ ጎሎልቻ 50፣ ጅንካ 31.6፣ 36.4፣ 30.7፣ ሆሳዕና 32.7፣ 33.2፣ ጃራ 50፣ ካቺሴ 105.2፣ ላሊበላ 39.2፣ 36፣ 46.9፣ ላሬ 48.7፣ 36፣ 46፣ ሊሙገነት 44.7፣31.5፣ 69፣ ማጂ 35.8፣ ንፋስ መዉጫ 36.1፣ ማይጨዉ 33.5፣ 43.2፣ ማጅቴ 36.1፣ ማንኩሽ 49፣ 59፣ 32.4፣ 33.4፣ ማሻ 70.4፣ 30.4፣ 30.2፣ 40.4፣ 30.6 መሃል ሜዳ 58.2፣ 54.6፣ 43.1፣ መኢሶ 47.5፣ 31.2፣ 52.1፣ መካነ ሰላም 34.5፣ 34.7፣ መተማ 31.9፣ 53.7፣ ሞጣ 81፣ 65፣ አዳማ 43.6፣ 59.4፣ 52.1፣ 88.3፣ ነጆ 64.1፣ ነራ ኤራ 32.6፣ 33.8፣ 79.4፣ ሰኮሩ 38፣ ሰንቃጣ 46.1፣ 68.9፣ ፓዌ 65.7፣ 30.9፣ ሽርቆሌ 35.2፣ ሲሪንቃ

Ethiopian Meteorology Institute

40.8፣ 35፣ 43.6፣ አቦሞሪንጋ 37.2፣ 34.6፣ ሻሁራ 44.8፣ 33.3፣ 56.6፣ ሽሬ 35.5፣ 70.5፣ 36፣ 49.3፣ 30.7፣ ሾላ ገበያ 57.1፣ ቴፒ 31.2፣ ተርጫ 37.8፣ 35.6፣ ጽጺቃ 52.6፣ ወገል ጤና 33.5፣ 36፣ 32፣ ወረኢሉ 44.9፣ 32.1፣ 39.7፣ አዲስ አለም 31.5፣ 32.5፣ አዲስ ዘመን 34.3፣ 42.2፣ 40፣ 42.3፣ 35.2፣ 32፣ 45.1፣ 30፣ አዲ አርቃይ 40፣ 31፣ 32.5፣ 40.8፣ 50.1፣ 85.5፣ 38.4፣ 37.9፣ 30፣ 38.5፣ አቃቂ 36.3፣ 55፣ 31፣ አሺ 32.6፣ 32.8፣ 32.4፣ አሸሪ 65.7፣ አሳሳ 46.5፣ አታንጎ 57፣ 33፣ 45.5፣ አዋሽ ሸለቆ 41.3፣ 46.3፣ 30.1፣ 32.3፣ ቢላምቢሎ 37.7፣33.5፣ 31.4፣ ቦቄሳ 48.5፣ ቦርቃ 40፣ 43.1፣ 49.2፣42.1፣ 44.6፣ ቡልቂ 30.5፣ ጨለንቆ 57.6፣ ጫጫ 32.6፣ 53.6፣ ጨፌ ዶንሳ 48.4፣ 50.3፣ 52፣ 30.3፣ ምንደር ሰባት 31.3፣10.7፣ ደበሌ 33.1፣ ደብረ ሲና 39.1፣ 50.4፣ 74.4፣ 31.7፣ 30.7፣ 68፣ 37.6፣ ደጀን 55.8፣ ደጋን 32፣ 74.8፣ ደነባ 54.1፣ ደንግጎ 31.9፣ ደንጎለታ 46.4፣ 46.4፣ 31.4፣ ደራ 45፣ 30፣ 30.5፣ 35.5፣ ዲንሾ 33፣ ጁሩ 48.1፣ እንዳባጉና 31.3፣ እብናት 30፣ 30.6፣ እርምጭ 46፣ ፈረስ ቤት 31.2፣ 41፣ ጋሸና 55.4፣ 34.2፣ 51.1፣ 34.2፣ 34.8፣ 80.9፣ 32.9፣ ጊናገር 35.7፣ 38.9፣ 40.7፣ 32.8፣ 35.9፣ ጊሸ ራቢል 34.4፣ ጉበይሬ 37.9፣ 56.3፣ 60.3፣ 42.2፣ 39.6፣ 54.5፣ 39.5፣ 45.9፣ 38.9፣ 30.5፣ 36.4፣ 43.5፣ 43.5፣ 48.3፣ 40.2፣ ጉጉፍቱ 64.2፣ ሀገረ ሰላም 34.7፣ ሃርቡ 32.3፣ ሃሮ 50.2፣ 60.2፣ 50.2፣ 30.2፣ 40.8፣ 40.2፣ 50.2፣ 52.2፣ 60.4፣ 70.2፣30.2፣ ሃሪ 30.2፣ 40.5፣ ሃራ 34፣ 48፣ 30.3፣ 56፣ ሂርና 50.2፣ 59.4፣ 42.5፣ 30.2፣ ሆርዶዮ 70.2፣ 32.1፣ 31፣ ጅሁር 37.5፣ ካራሚሌ 51.4፣ 30.8፣ 91.8፣ 42.8፣ 50.6፣ 79.8፣ ቀርሳ 34.8፣ 75.1፣ 34.2፣ 35.6፣ ቁልምስቅ 37.3፣ 31.1፣ ቁሉቢ 32.5፣ 37.6፣ 47.5፣ 34.5፣ 60.5፣ 54.5፣ 37.5፣ ቅዳሜ ገበያ 57.6፣ 37.6፣ 36.9፣ 58.8፣ 47.9፣ 47.9፣ 33.8፣ ኮሶበር 30፣ ኩሚ 64.5፣ 110፣ 53.5፣ 31.6፣ 30.3፣ 42.6፣ ኮበን 33፣ 31፣ 37.5፣ 37.5፣ ሊበን 47.4፣ 35.2፣ ላሎ ቂሌ 39.2፣ መካነ ኢየሱስ 38.3፣ 41.8፣ መልካ ጀበዱ 38.8፣ 37.4፣ 61.8፣ ማርዬ 45.6፣ 62.5፣ 43.3፣ ማያንሳ 43.2፣ 30.1፣ መንዲዳ 34.2፣ 44.3፣ 33.1፣ መርሳ 32.8፣ 54.2፣ 35.4፣ 42.6፣ 55.6፣ መርጦ ለማርያም 37.5፣ ሞላሊ 34.3፣ 41.9፣ 34.3፣ ሙጊ 57፣ 45.7፣ ሙጃ 30.3፣ 36.8፣ ኖፓ 43.5፣ ሮብ ገበያ 32.8፣ ሮቢት 33.1፣ 32.5፣ 39.5፣ 48፣ 49.2፣ 35፣ 53.2፣ 37.3፣ ሰዲቃ 35.6፣ ሰቆጣ 35.6፣ 32.5፣ ተርኮዲ 33.2፣ 33.7፣ 34.7፣ 32.5፣ 70.7፣ ትንሹ መጢ 56.1፣ 40.7፣ 32.6፣ ጽገሬዳ 41.1፣ ወግዲ 36.3፣ ዉቅሮ 56፣ 30፣ 34፣ 36፣ ያንፋ 35.3፣ 35.2፣ 40.1፣ 33.2፣ 40.3፣ 40.6፣ 30.3፣ 30.336.5. 32.4፣ ያዮ 30.6፣ 45.8፣ 31.4፣ ይችላ 49.8፣ ምንደር አስራ አንድ 60፣ 39.5፣ 36.5፣ 40፣ 32.5፣ 45፣ 39፣ የሪ 35፣ 65፣ 45፣ 45፣ 125፣ 30፣ 30፣ 30፣ ወልዲያ 32.1፣ ሲቦ 43.4፣ ዉቅሮ ማሪያ 35.2፣ 39.4፣ 40.3፣ 32.8፣ ኢዳግ አርቢ 30.4፣ 40.2፣ 45.3፣ 32.5፣ 35.2፣ 47.5፣ 42.6፣ 40.8፣ 36.4፣ አዋሽ ሰባት 32.2፣ ጎበዬ 37.9፣ 56.3፣ 60.3፣ 42.2፣ 39.6፣ 54.5፣ 39.5፣ 45.6፣ 30.2 አንኮበር 40፣


41፣ 31.1፣ 70 30፣ 40፣ 33.1፣ 47፣ 36.2፣ 45.1፣ 38 እንዲሁም መቀሌ ኦብዞርባቶሪ 33፣ ሚ.ሜ ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፈዉ የኦገስት ወር በ185 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 60.3 - 167.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ70 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ነቀምት፣ የራ፣ ኩሚ፣ ካቺሴ፣ ካራሚሌ፣ አዳማ፣ ኢጃጂ፣ አዲዓርቃይ፣ ሞጣ፣ ጋሸና፣ ደባርቅ፣ ኑራ ኤራ፣ ቀርሳ፣ ዲጋን፣ ጨለንቆ፣ ደበረ ሲና፣ ተረኮዲ፣ ሽሬ፣ ማሻ፣ ሃሮ፣ ሆሮ ዶዮ፣ ጭፍራ፣ ሀይቅ፣ አንኮበር ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከኦገስት 1-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ70 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉዉ ኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ ምዕራብና ምስራቅ ሓረርጌ፤ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎ የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ151-70.3 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ13-31 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ጥቂት የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣ ላይ ከ61-150 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-16 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስር 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉዉ ኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሊባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሓረርጌ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ጉጂ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎና የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ ጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ እና የሊበን ዞኖች፣ ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኦገስት ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግብርናው የስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተለይም በማደግ፣ በማበብና ፍሬ በመሙላትም ላይ ባሉ ለረጅም፣ ለመካከለኛ እና ለአጭር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች

የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦት በተሻለ ሁኔታ እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የጎርፍ ክስተቶች፣ የመሬት አቀማመጣቸው ከፍተኛና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት፣ መሰንጠቅና ናዳ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡


በተለይም በገዋኔ ወረዳ የጣለው ከባድ ዝናብ በእንስሳት ላይ ጉዳት አድርሷል፤ በዋግህምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ጋዝጊብላ ወረዳ በረዶ ቀላቅሎ የጣለው ከባድ ዝናብ በተዘሩ ሰብሎች ላይ ጉዳት አድርሷል፤ በሸሬ ከተማ እና ቢሾፍቱ ከተማ የጣለው ከባድ ዝናብ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፤ በምሁር አክሊል ወረዳ መገራን ቀበሌ ላይ በነበረ የጎርፍ እና የመሬት ናዳ በንብረትና በሰብል ላይ ጉዳት አድርሷል፤ በጋምቤላ ክልል በተከሰተው የጎርፍ አደጋ በተዘሩ ሰብሎችና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ኤፍራታና ግድም ወረዳ ከባድ ነፋስ ቀላቅሎ የጣለው ዝናብ ባስከተለው ጎርፍና በተከሰተው የመሬት መንሸራተት በሰዎች ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፤ በከምባታ ዞን በአንጋጫ ወረዳ በዞቤቾ ቀበሌ በመሬት መንሸራተት አደጋ በሰዉ ህይወት፣ እንዲሁም በጌዴኦ ዞን በራጴ ወረዳ ለሁለት ተከታታይ ቀናት የጣለዉን ከባድ ዝናብ ተከትሎ በጨራቃ ቀበሌ  የመሬት ናዳ ተከስቶ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 4 )።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦገስት ወር በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አይሻ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በላይኛው እና በመካከለኛው አባይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ መሻሻል ጥሩ አስተዋፅኦ እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ዝቅተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን ይህም በተፋሰሶቹ ላይ በቂ የውኃ ፍሰት እንዳይኖር በማድረግ ረገድ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 5)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ


በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ። በዚህም መሠረት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም ከ12-23 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ከ3-15 ቀናት ያህል ከ20-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ስፍራዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የሚጨምር በመሆኑ 30-100 ሚ.ሜ ከ3-12 ቀናት ይደርሳል፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

በመደበኛው ሁኔታ የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች የፀሐይ አቅጣጫን ተከትለው ከሴፕቴምበር የመጀመሪያው ሳምንት በኋላ ከሰሜንና ሰሜን ምሥራቅ አካባቢዎች የሚዳከሙ ሲሆን በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና መካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በወሩ መጨረሻ ሳምንት ደግሞ ዝናብ ሰጪ ክስተቶቹ እየተዳከሙ በመምጣት ከአብዛኛዎቹ የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛውና ምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ ተፅዕኖ ስር መሆን ይጀምራሉ።

በመጪው ሴፕቴምበር በምዕራብ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ ኦሮሚያ ምዕራባዊ አጋማሽ ላይ የክረምቱ ዝናብ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል ሲሆን፤ በመጠን ረገድ ደግሞ አብዛኛው ትግራይ፤ የአማራ ምሥራቃዊ አጋማሽ፤ በመካከለኛው ኦሮሚያ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት አካባቢዎችን ጨምሮ መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በተለይ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም የምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች፣ የሶማሌ ማዕከላዊ እና ደቡባዊ ክፍል፣ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እንዲሁም ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ እንዲሁም የአፋር ደቡባዊው ክፍል ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ መጠኑም ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እንደሚሆን ይጠበቃል። በሌላ በኩል ደግሞ የክረምት ዝናብ ሰጪ ክስተቶች አልፎ አልፎ ወደ ደቡብ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ ከደቡብ ኦሮሚያ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች አልፎ አልፎ ዝናብ

የሚያገኙ ሲሆን፤ የደቡብ ሶማሌ አካባቢም በወሩ መጨረሻ ላይ አነስተኛ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-30/ 2025 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

## 2.2 እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የመስከረም ወር በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ  በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ ለግብርናው ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች፣ ለፍራፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት መጠን ከማሟላት አንጻር ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በአንፃሩም የእርጥበት ሁኔታው በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ወደ ሆኑት የሀገራችን አካባቢዎች የሚኖረው መስፋፋት የማሳ ዝግጅት ለማድረግና የበጋ ወቅት ሰብሎችን ለመዝራት እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመሬት መንሸራተት እንዲሁም በተዳፋትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር መሸርሸርና በእርሻ ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት እና በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስቀድሞ

ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድረግ አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እና ውሃ አጠር ለሆኑና የተለያየ ዘዴን ተጠቅመው ውሃን ለሚያቅቡ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከፍተኛ እርጥበት ጥሩ አጋጣሚ ሰለሚሆን አጋጣሚው መጠቀም ያስፈልጋል።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጭው የሴፕቴምበር ወር በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ሽፋንና ፍሰት ይጠበቃል፡ ፡ ይህም ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር የውሀ ፍሰትን በመጨመር ወደ ሰው ሰራሽም ይሁን የተፈጥሮ የውሃ መያዣዎችና ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከፍ እንደሚያደርገውና የውሃ ሀብትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል ባለፉት የክረምት ወራት ወደ ግድቦች የገባው የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ በቀጠይ ከሚጠበቀው ከፍተኛ የውሀ ፍሰት ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት ዝቅተኛና ረባዳማ ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍም ሆነ የወንዞች ከገደብ በላይ መሙላት በተለይም በተከዜ፣ በአባይ (በፊንጫና በጣና በለሥ ግድቦች) በኦሞ ጊቤና በላይኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ስጋት ሊፈጥር ይችላል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ ለመቀነስም ሆነ መልካም ዕድሎችን በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ-ሃሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡